# ከ COVID-19 ዝርያዎች ደህንነትዎን ይጠብቁ

**ቫይረሱ ሲለወጥ** (ሲቀየር)፣ አዲሱ ዓይነት ዝሪያ ተብሎ ይጠራል።
**የጸረ COVID-19 ክትባት መከተብ የዝሪያዎች ስርጭትን ለማስቆም ሊረዳ ይችላል።**



## ስለ COVID-19 ትክክለኛ ወሬ

### ስለ ዝሪያዎች ማወቅ የሚያስፈልጉ ነገሮች

- ብዙ ሰዎች በታመሙ ቁጥር፣ COVID-19 የሚያመጣው ቫይረስ ለመለወጥ ብዙ እድሎች ይኖሩታል እና **አዳዲስ ዝሪያዎች ይፈጠራሉ።** ክትባቶች ወደፊት ለሚፈጠሩ ዝሪያዎች ብዙ ውጤታማ ላይሆኑ ይችላል።
- አንዳንድ ዝሪያዎች **በጣም በፍጥነት ሊሰራጩ** እና **ሰዎችን ሊያሳምሙ** ይችላሉ።.
- ዝሪያው ሲሰራጭ ብዙ ሰዎች **በጣም ሊታመሙ ወይም ሊሞቱ** ይችላሉ።
- **ብዙ ቁጥር ያላቸው ሰዎች ሲከተቡ፣ ከዝሪያዎቹ የሚጠበቁት** ሰዎች ቁጥር ብዙ ይሆናል።

### ክትባቶች ዝሪያዎችን ማስቆም ሊረዱ ይችላሉ

- የዝሪያዎችን ስርጭት ለማስቆም **ተመራጭ ከሆኑ መንገዶች** ውስጥ አንዱ የ **COVID-19 ክትባት መውሰድ** ነው።
- የ COVID-19 **ክትባቶች** የሚታወቁ ዝሪያዎች ላይ **አስተማማኝ እና ውጤታማ** ናቸው።

### የራስዎን እና የሌሎችን ደህንነት ይጠብቁ

- **የ COVID-19 ክትባት የወሰዱ የረጅም ጊዜ እንክብካቤ ተቋም ሠራተኞች፣** የራሳቸውን፣ የቤተሰቦቻቸውን እና የታካሚዎቻቸውን **ደህንነት** ይጠብቃሉ።
- **በእድሜ የገፉ ወይም የሰውነት የበሽታ መከላከል ዓቅማቸው የተጎዳ ሰዎች** በ COVID-19 ምክንያት ለሚመጡ ውስብስብ ችግሮች ከፍተኛ ተጋላጭ ናቸው።

**ነጻ ክትባትዎን ያግኙ!**